ሳምንት 12

4ኛ ክፍል

# የፆታ እኩልነት

Leveled



Amharic

ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2009 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*

# የፃታ እኩልነት

4ኛ ክፍል | ሳምንት 12 | Leveled



## የመምህራን ማስታወሻ

ይህ መጽሀፍ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት የንባብ ክሂልን ለማሳደግ እና ልጆች ጥሩ የተዘጋጀ ነው። ተማሪዎች ይህንን መጽሀፍ ተጠቅመው የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ የወላጆች ና የመምህሮች እገዛና ክትትል እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። መምህሮች፣ በመጽሀፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን በተገቢ መንገድና በትክክል በማንበብና በማስነበብ ድርሻችሁን ልታበረክቱ ይገባል። የተከበራችሁ መምህራን እና ሌሎች አጋዥ አንባቢዎች፣ ይህንን መጽሀፍ ለተማሪዎች ከማንበባችሁ በፊት በግላችሁ አንብቡና ሀሳቡን በመረዳት በቂ ዝግጅት አድርጉ።

**መፅሀፉን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን ስጡ።**

1. የፆታ እኩልነትን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?
2. በቤተሰባችሁ ውስጥ ምን ዓይነት ሥራዎችን ትሰራላችሁ? ለምን?
3. በሥራቸው ታዋቂ የሆኑ ሴቶችን ታውቃላችሁ? ምን ምን ተግባራትን ፈፅመው የታወቁ ይመስሏችኋል?



## ምዕራፍ አንድ፡ የወይዘሮ ነኢማ ጥድፊያ

ዛሬ እለቱ ሰኞ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው:: ሀዋና አደም እህትና ወንድም ናቸው:: በጧቱ ተነስተው ወደትምህርትቤት ለመሄድ ይዘጋጃሉ:: እናታቸው በማዕድ ቤት ስራ ተጠምደው ልጆቻቸውንና ባለቤታቸውን ቁርስ ሊያበሉ ጉድ ጉድ ይላሉ:: አባታቸውም ወደሥራ ለመሄድ የሥራ ልብሳቸውን በመለባበስ ጫማቸውን ይጫማሉ:: የእነሀዋ እናት ወይዘሮ ነኢማ አንዴ ፓስታውን ሲሰሩ፣ አንዴ ደግሞ ወተቱን ሲያፈሉ፣ ጊዜው አልበቃቸው ብሎ ከመጠን በላይ ይጣደፋሉ::



## ምዕራፍ ሁለት፡ የሀዋና የወይዘሮ ነኢማ ውይይት

ወይዘሮ ነኢማ “ሀዋ! ሀዋ” ሲሉ ተጣሩ፡፡ ሀዋም “አቤት እማዬ ምን ሆነሽ ነው?” በማለት እየሮጠች ወደማዕድ ቤት ሄደች፡፡ እናቷም “ይውልሽ ወተቱ ሊገነፍልብኝ ስለሆነ አንቺ የፓስታውን ሽንኩርት አቁላይው፤ እኔ ደግሞ ወተቱን አፍልቼ ላውጣው” አሏት፡፡ ሀዋም “እማዬ የደንብ ልብሴን አለበስኩም፤ ደብተሬንም አላዘጋጀሁም እኮ!” አለቻቸው፡፡ እሳቸውም “ወንድምሽን ጥሪና ንገሪው፤ ደብተርሽን በቦርሳሽ ውስጥ ይከትልሻል” አሏት፡፡

“እንዴት እማዬ! አደም እንዴት አድርጎ ነው የእኔን ደብተር በቦርሳዬ የሚከተው? ሁሉንም ደብተሮቼን ይዤ እኮ አልሄድም፤ በመርሃግብሩ መሰረት ዛሬ የምንማራቸውን ደብተሮችና መፅሃፎች ብቻ ነው ይዤ የምሄደው::
እኔና አደም የክፍል ደረጃችን አንድ ስላልሆነ ዛሬ ምን እንደምንማር አያውቀውም” አለቻቸው:: “ያም ሆነ ይህ አሁን ያዘዝኩሽን ስራ ስሪ፤ ለትምህርቱ እንደሆነ ትደርሽበታለሽ” አሏት::

ሀዋና እናቷ እንደዚህ እየተነጋገሩ እያለ ወተቱ በመፍላቱ ወይዘሮ ሀዋ ቀስ ብለው ካወጡት በኋላ ወደመመገቢያ ክፍል ወስደው ሲመለሱ ሀዋ የፓስታውን ሽንኩርት ስታቁላላ አገኟት:: እሳቸውም በሽንኩርቱ ላይ ዘይት፣ ቲማቲም፣ በርበሬ በመጨመር በደንብ ካቁላሉ በኋላ ከተቀቀለው ፓስታ ጋር አዋሃዱና በፓስታው ማቅረቢያ እቃ ላይ አደረጉ::
ሀዋ በየሳህኑ የተደረገውን ፓስታ ይዛ ወደመመገቢያ ክፍል ሄደች::

በመቀጠል የወተት መጠጫ ኩባያዎችን አጣጥባ አቀረበች:: እናቷም ሹካዎችንና ማንኪያዎችን ይዘው ሄዱ::

ከመመገቢያ ክፍሉ እንደደረሱ ልጃቸው አደምና ባለቤታቸው አቶ ሙስጠፋ ቁርስ ለመብላት በምግብ ጠረጴዛው ባሉት ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ሲጠባበቁ አገኟቸው፡፡ ሀዋ ምግቡን በማቀራረብ እናቷን ካገዘች በኋላ የደንብ ልብሷን ለመለባበስና ደብተሯን ለመያዝ ወደመኝታ ክፍሏ እየሮጠች ሄደች፡፡

አደምና አቶ ሙስጠፋ ቁርሳቸውን እያጣጣሙ እየተመገቡ "ያቺ ልጅ ቁርሷን አትበላም እንዴ? የትምህርትቤት መግቢያ ሰዓት እየረፈደባት እኮ ነው" አሉ፡፡ ወይዘሮ ነኢማም "ምን ታድርግ እኔ ቁርስ ሳዘጋጅ ስራ በዛብኝና እንድትረዳኝ ጠራኋት፤ እሷ ባታግዘኝ ኖሮ የእናንተም ሰዓት ይረፍድባችሁ ነበር!" በማለት ተናገሩ፡፡ አቶ ሙስጠፋም "በጧት ብትነሱ ኖሮ ጊዜያችሁን ባግባቡ ትጠቀሙ ነበር፡፡ ይኸው እኛ ተዘገጃጅተን ቁርስ ለመብላት የተቀመጥንበት ሰዓት እንኳ በጣም ብዙ ነው" አሉ፡፡

ወይዘሮ ነኢማም “ወይ ጉድ አንተና አደም ምን ሥራ ትሠራላችሁ፤ በጧት ተነስታችሁ የግል ንፅህናችሁን ከጠበቃችሁ በኋላ ልብሳችሁን ለብሳችሁ፣ ቁርሳችሁን በልታችሁ መውጣት ነው” አሉ።

አደምም “እማዬ እኔም እኮ እንደሀዋ ሥራዎችን ላግዝሽ እችል ነበር፤ አባዬና አንቺ ግን ‘ይሄ የሴት ሥራ ነው፤ አንተ ማዕድቤት ለማዕድቤት ምን ያስኬድሃል’ እያላችሁ ትገስፁኛላችሁ” አላቸው።

እናቱም “አዎ ልጄ! ጥፋቱ የእኔና የአባትህ ነው። አባትህ በፆታ እኩልነት ለማመን ይቸገራል። እኔም ቢሆን የተለያዩ ሁኔታዎችን ከጎረቤትም ሆነ ከመገናኛ ብዙሃን ባዳምጥም አስተዳደጌ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል” አሉት። አቶ ሙስጠፋም “እኔ የውጪውን ሥራ ስሰራ እውላለሁ፤ አንቺ ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን ሥራ ሰርተሽ ብትጠብቂ ምን ችግር አለው?” አሉ።

በዚህ ጊዜ ሀዋ የደንብ ልብሷን ለብሳ፣ የደብተር ቦርሳዋን ይዛ ወደመመገቢያው ክፍል ገባች።

ሁሉም “ነይ፣ ቁርስሽን ብይ” አሏት። ሀዋም “ረፍዷል እኮ! እማዬ አንድ ሁለት ጊዜ ያህል አጉርሽኝና ልሄድ” አለቻቸው።

እናቷም ፓስታውን በሹካ እየጠቀለሉ በቁሟ ያጎርሷት ጀመር፤ ወተቱንም እያባረዱ አጠጧትና አፏን ተጉመጥምጣ ከወንድሟ ጋር ተያይዘው ወደትምህርትቤት ሄዱ።

አቶ ሙስጠፋም ምግቡን ተመግበው ከጨረሱ በኋላ ከዘራቸውን ይዘውና ጋቢያቸውን ለብሰው ወደሱቃቸው ሄዱ ወይዘሮ ነኢማም የቁርስ መመገቢያ እቃዎችን ካነሳሱ በኋላ ቤቱን ያፀዱ ጀመር። ቤቱን ከጠራረጉ በኋላ እቃዎችን አስተካክለው አስቀመጡ፤ የእነሱንና የልጆችን አልጋዎች አነጠፉ። ልብሶችንም አጣጥፈው በቁምሳጥንና በሳጥን አስቀመጡ። ከዚያም ምሳ ለማዘጋጀት ወደማዕድቤት በመሄድ ሽንኩርት ከታትፈው በሁለት ምድጃ ቀይና አልጫ ወጥ ሠሩ።



## ምዕራፍ ሦስት፡ የወይዘሮ ነኢማ የሥራ ጫና

ወይዘሮ ነኢማ ወጥ ከሠሩ በኋላ ግቢውን በሚገባ አፀዱ። በመቀጠል የቡና እቃዎችን በማቀራረብ ቡናቸውን አፈሉ። አሁን ከቀኑ 11፡30 ሆኗል። ወይዘሮ ነኢማ የመክሰስ እቃዎችን፣ እንጀራውንና ወጡን በማቀራረብ በር በሩን እያዩ መጠባበቅ ጀመሩ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ አቶ ሙስጠፋ "እንደምን ዋልሽ?" እያሉ ወደእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ።

ወይዘሮ ነኢማም የባለቤታቸውን የሰላምታ አፃፋ ከመለሱ በኋላ በመመገቢያው ቦታ እንዲቀመጡ ጋበዟቸው። ልጆቹም ከትምህርትቤት እየተሯሯጡ መጥተው የእናታቸውን አንገት አቅፈው ግራና ቀኝ ጉንጫቸውን ሳሟቸው፤ በመቀጠል ወደአባታቸው በመሄድ የአባታቸውን ጉልበት ለመሳም ዝቅ ሲሉ "እረ አይገባም! ኑ ጉንጬን ሳሙ" አሏቸውና ጉንጫቸውን ሳሟቸው። ወይዘሮ ነኢማም "በሉ

ቁጭ በሉ መክሰስ ላምጣላችሁ” አሉና “ሀዋዬ በይ ቦርሳሽን አስቀምጪ፤ የደንብ ልብስሽንም ቀይሪና ምግብ ማቀራረቡን እርጂኝ” በማለት ወደጓዳ ገቡ።

ሀዋ የስራ ልብሷን ለበሰችና እናቷን ልታግዝ ወደማዕድቤት ሮጠች። አደምና አቶ ሙስጠፋም ወደየመኝታክፍላቸው ከሄዱ በኋላ ልብሳቸውን ቀያይረው መክሰሳቸውን ሊበሉ ተመለሱ። ዳቦው፣ ፓስታው፣ ወተቱ በጠረጴዛ ላይ ተደርድሮ ሲያዩት በጣም ተደሰቱ። የቤተሰቡ አባላት ተቀምጠው መክሰሳቸውን ከበሉ በኋላ ወተታቸውን እየጠጡ መጫወት ጀመሩ።

ትንሽ እንደተጫወቱ አቶ ሙስጠፋ “አደም የጥናት ሰዓትህ ደርሷል፤ ጨዋታው ይብቃህና ወደጥናትህ ሂድ!” በማለት አሳሰቡ። አደምም “አባዬ ሁልጊዜ እኔን ብቻ አጥና የምትለኝ ለምንድን ነው”? ሀዋም እኮ ማጥናት ይገባታል?” አላቸው። ሀዋም “አዎ! አባዬ እኔን አንድም ቀን ሂጂና አጥኚ ብለሽኝ አታውቅም” አለቻቸው። አባትዬው ያልጠበቁት ነገር በመሆኑ በጣም ከመደንገጣቸው የተነሳ አፉቸውን በእጃቸው ይዘው አንዴ አደምን አንዴ ደግሞ ሀዋን ይመለከቱ ጀመር።



## ምዕራፍ አራት፡ የሀዋ ቤተሰብ ስለውጥ መዘጋጀት

ወይዘሮ ነኢማም የአደም ጥያቄና የሀዋ ንግግር ስሜታቸውን በጣም ነካው:: እናትም፣ አባትም የማዕድቤት ስራን የሚያዙት ሀዋን እንጂ አደምን አልነበረም:: ሁለቱም ልብ ብለው ሳያስተውሉት ምን ያህል በሴት ልጃቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደፈጠሩ ዛሬ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለማስተዋል በቁ:: አቶ ሙስጠፋም ሴት ልጃቸውን ብቻ ሳይሆን ባለቤታቸውንም ምን ያህል የቤቱን ሥራ በሙሉ እንዲሰሩ በማድረግ ጫና የፈጠሩባቸው መሆኑ በጣም ተሰማቸው::

ሀዋና አደም ለጥያቄያቸው ምላሽ ሲጠብቁ፣ አቶ ሙስጠፋና ወይዘሮ ነኢማ ደግሞ ከህሊናቸው ጋር ሲሟገቱ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ:: አቶ ሙስጠፋ እንደመሳል አሉና ጉሮሯቸውን ከጠራረጉ በኋላ “ልጆቼ የተናገራችሁት ነገር ውስጤን በጣም አስደንግጦታል:: ሁለታችሁም ውድ ልጆቼ ናችሁ:: ሀዋ የማዕድቤት ሥራ እንድትሰራ አንተ ደግሞ እንድታጠና አድልቼ አይደለም:: ካንተ ይልቅ ሀዋ እናቷን ለመርዳት ስለምትፈልግና እናቷም እሷ እንድታግዛት ስለምታደርግ ነው” በማለት ተናገሩ::

ወይዘሮ ነኢማም “እኔ ሀዋን እንድታግዘኝ ስለምፈልግ አይደለም ሁልጊዜ የምጠራት በለመድኩትና ባደግሁት ወግና ልማድ ውስጥ ስላለሁ ብቻ ነው እንጂ፣ እኔም ሆንኩ ሀዋ የማዕድቤት ሥራ እንድንሰራ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች የሉም:: ሁላችንም ተጋግዘን ሥራችንን መሥራት ይገባናል:: ለሀዋም እንደአደም ትምህርቷን በሚገባ እንድትከታተል እድል ልንሰጣት ይገባል:: እኔም ብሆን የቤቱን ሥራዎች በሙሉ ብቻዬን መሥራት የለብኝም::

ቀኑን ሙሉ እረፍት ሳይኖረኝ ቁርስ፣ ምሳና ራት ስሰራ፣ ቤትና ግቢ ሳፀዳ፣ ሌሎችንም ሥራዎች ስሰራ ጀንበር ወጥታ ትጠልቃለች።

አንዳንዴ ሲደክመኝ ሀዊ እንድታግዘኝ እጠራታለሁ፤ ይህን በማድረጌ በጥናቷ ላይ ጫና እንደማሳድርባት አልጠፋኝም። ነገርግን አማራጭ ስለሌለኝ ነው" በማለት ተናገሩ። አደምም "አሁን ያለፈው አልፏል፤ ለወደፊቱ ምን እናድርግ? በሚለው ብንወያይ ጠቃሚ ይመስለኛል" አለ።

አቶ ሙስጠፋም "አዎ! ያለፈው አልፏል፤ አሁን ማድረግ የሚገባንን ማድረግ ነው" አሉ። ሀዊም "አባዬና አደም ወጥ መሥራት፣ ቡና ማፍላት፣ ግቢ ማፅዳት፣ አልጋ ማንጠፍና ቤት ማዘጋጀት መልመድ አለባችሁ" አለቻቸው። እኔ አደምንም አለማምደዋለሁ፤ እማዬ ደግሞ አባዬን አለማምጂውና ከዚያ በኋላ የሥራ እቅድ አውጥተን በእቅዳችን መሠረት ስራችንን እናከናውናለን" በማለት ተናገረች።

በማግስቱ ቅዳሜ ሀዊ ወንድሟ አደምን የአልጋ አነጣጠፍ፣ የቤት አጠራረግ፣ የእቃ አስተጣጠብ ስታስተምረው ዋለች። ወይዘሮ ነኢማም አቶ ሙስጠፋን የሽንኩርት አከታተፍን፣ የወጥ አሰራርን አለማመዷቸው።

እሁድ እለት ሁሉም በጧት ተነሱና አሁንም ልምምዱን ቀጠሉ:: አደም አልጋ ማንጠፍ፣ ቤት መጥረግና እቃ ማጠብ በፍጥነት ተለማመደ:: አቶ ሙስጠፋም ሽንኩርት ሲልጡና ሲከትፉ ዓይናቸውን ትንሽ ቢያቃጥላቸውም ብዙ አልተቸገሩም::

ከአንድ ሳምንት ልምምድ በኋላ የቤተሰቡ አባላት በጋራ በመወያየት የስራ እቅድ አወጡ:: አቶ ሙስጠፋና ወይዘሮ ሀዋ እየተጋገዙ ቁርስ ያበስላሉ:: አደምና ሀዋ ደግሞ አልጋ ያነጥፋሉ፤ ቤት ይጠርጋሉ፤ እቃም ያጥባሉ:: ይህንን የዘወትር ተግባራቸውን በፍጥነት በማከናወን ጊዜያቸውን ባግባቡ መጠቀም ቻሉ:: ወይዘሮ ነኢማ በቤት ውስጥ በመዋል የቤት ውስጥ ስራ ብቻ በመስራት ዓመታትን ቢያስቆጥሩም አሁን ግን ባለቤታቸውንም ለማገዝ ወደሱቅ መሄድ ጀምረዋል::

በሱቁ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በመቆየት የንግድ ስርዓትን ተለማመዱ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ አጉል ባህልና ልማድ ያቆያቸውን የስርዓተ ፆታ ተፅዕኖ ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት አደረጉ:: በዚህም የተነሳ የእነሀዋ ቤተሰቦች ደስተኞች ሆኑ::



## ምእራፍ አምስት፡ የአቶ ሙስጠፋና የጓደኛቸው ክርክር

ዛሬ ቀኑ እሁድ የሳምንቱ መጨረሻ ቀን ነው። የአቶ ሙስጠፋ ጓደኛ ወደእነአቶ ሙስጠፋ ቤት መጡ። ከዚያም "አቶ ሙስጠፋ! እዚህ ቤት! እንደምን አደራችሁ?" እያሉ የቤቱን አጥር በር ያንኳኳኩ ጀመር። አቶ ሙስጠፋና ወይዘሮ ነኢማ ልብስ ሲያጥቡ ልጆቹ ደግሞ ቤት ያፀዱ ነበር። አደም እየሮጠ ሄዶ የአጥሩን በር ለሰውዬው ከፈተላቸው። ሰውዬውም ወደግቢ ሲገቡ ባዩት ነገር በጣም ተደመሙ። ቀጥለውም "እንዴ! እንዴ! ሙስጠፋ ምን እያደረግህ ነው? ነኢማና ልጆች ልብስ ለማጠብ አልበቃ ብለው ነው?" አሉና በመገረምና በቁጣ አቶ ሙስጠፋን ጠየቁ።

አቶ ሙስጠፋም "ይህ አስተሳሰብ እኮ ድሮ ቀረ። እኔም እንዳንተ ወጥ መስራት፣ ልብስ ማጠብ፣ ግቢ ማፅዳት፣ እቃ ማጠብና ሌሎች የቤት ውስጥ ስራዎች የሴቶች ብቻ ይመስለኝ ነበር። መሳሳቴን ልጆቼ ነገሩኝ። አንዳንድ

የሰፈራችንን ሰዎች በምሳሌነት እያነሱ አስረዱኝ፡፡ እኔም አመለካከቴ ትክክል አለመሆኑ ገባኝ፡፡ የምንሰራው ሥራ የወንድና የሴት ተብሎ በተፈጥሮ የተሰጠን አይደለም፤ እኛ ራሳችን የፈጠርነው ችግር እንጂ!” በማለት ተናገሩ፡፡

ጓደኛቸውም “በልብሱ ማጠብ ስገረም ሌላም የማዕድቤት ሥራ ትሰራልኛለህ!” አሉ፡፡ አሁንም ከዘራቸውን ወደፊት አንስተው ወደአቶ ሙስጠፋ እያመለከቱ፡፡ ወይዘሮ ነኢማም “ወንድ ወደችሎት ሴት ወደማጀት” የሚለው አባባል ያለፈበት፣ ሴትን የሚበድል መሆኑ ከተረጋገጠ ቆይቷል፡፡ አሁን ሴትም ሆነ ወንድ የሚለየን ፆታዊ አፈጣጠራችን እንጂ የምንሰራው ተግባር አይደለም፡፡ እናንተም ምግብን ሠርታችሁ መመገብ ትችላላችሁ፤ እኛም መነገድ፣ ማስተማርና ሌሎች የውጪ ስራዎችን መሥራት እንችላለን፡፡

ዋናው ቁምነገር ተሳስቦና ተጋግዞ ስራዎችን በማከናወን ኑሮን በጋራ ለማሸነፍ መጣር ነው፡፡ ሙስጠፋ ልብስ ስላጠበ ወይም ምግብ ስላበሰለ ሰብአዊነቱን የሚያሳጣው ነገር የለም፡፡ እኔም አብሬው ሄጄ ሸቀጣሸቀጦችን በመሸጥ ባግዘው ትዳራችን የተቃና ይሆናል እንጂ አይፈርስም” አሏቸው፡፡

የአቶ ሙስጠፋ ጓደኛ ጥቂት እንደማሰብ ብለው ከባልና ሚስቱ አጠገብ በወንበር ላይ ተቀመጡና ባልና ሚስቱ እየተረዳዱ ብዙ ልብሶችን በአጭር ጊዜያት ውስጥ ሲያጥቡ ተመለከቱ::

እነአቶ ሙስጠፋም ከእንግዳው ጋር ብዙ ነገሮችን እያነሱ ተጫወቱ:: በተለይ ስለፆታ እኩልነት ሲወያዩ ዋሉ:: እንግዳውም ከዚህ በኋላ ባለቤታቸውንም ሆነ ሴት ልጆቻቸውን ከራሳቸውና ከወንድ ልጆቻቸው ጋር እኩል እንደሚያዩዋቸው ተናገሩ:: የተለያዩ ተግባራትንም በጋራ ለማከናወን የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች ከእነአቶ ሙስጠፋ ተማሩ:: በመጨረሻም ይህንን ሁኔታ ዛሬውኑ ለቤተሰቦቻቸው ተናግረው ማሳመን እንዳለባቸው ቃል ገብተው ወደቤታቸው ሲሄዱ እነሱ ደግሞ ጨዋታቸውን ቀጠሉ::

የአቶ ሙስጠፋ ጓደኛ ቤታቸው እንደደረሱ ከዚህ በፊት ያላስተዋሉትን አሁን ግን በዓይናቸው ያዩትንና በጣም ያዘኑበትን ነገር ተመለከቱ:: ባለቤታቸው እንጀራ ሲጋግሩ፣ ትልቋ ልጃቸው ወጥ ትሰራለች፣ ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው ኳስ ይጫወታሉ:: ሌላዋ ሴት ልጃቸው ደግሞ እቃ ታጥባለች::

የአቶ ሙስጠፋ ጓደኛ ፈጠን ፈጠን ብለው ወንዶች ልጆቻቸው ወደሚጫወቱበት ሄዱና ጨዋታቸውን እንዲያቆሙ ነገሯቸው። ልጆቹም “አባዬ! አሁን እኮ ነው ከጥናት ክፍላችን የወጣነው” አሉ። አባትዬውም እንደሱ ብዬ አይደለም፤ ኑ እህታችሁን እቃ በማጠብ እርዷት” አሏቸው።

ልጆቹም “እንዴ አባዬ! እኛ አጥበን አናውቅም እኮ!” አሉ። አባታቸውም “እኔ አሳያችኋለሁ” ብለው እቃ ወደምታጥበዋ ልጅ ይዘዋቸው ሄዱና እቃውን እያጠቡ አሳዩአቸው። ልጆቹም በጣም እየተደሰቱ እቃውን በጋራ አጥበው ጨረሱ። እናትዬዋና ትልቋ ሴት ልጅም ሥራቸውን እንዳበቁ በእንግዳ መቀበያ ክፍል ተሰባስበው ተቀመጡ። አባትዬውም ዛሬ በእነአቶ ሙስጠፋ ቤት ያዩትን ነገር ሁሉ አብራርተው ነገሯቸው። የቤተሰቡ አባላትም ከነገ ጀምሮ ሥራዎችን ተከፋፈለው ሁሉም በአቅማቸውና በችሎታቸው መጠን እንደሚሰሩ ተማመኑ።

**በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን ስጡ።**

1. ወይዘሮ ነኢማ ቁርስ ለማዘጋጀት ምን ምን ተግባራትን አከናወኑ?
2. ወይዘሮ ነኢማ ሀዋን የጠሯት ለምንድን ነው?
3. የሀዋ ቤተሰቦች በሀዋ ላይ ያደረሱት አሉታዊ ተፅእኖ ምንድን ነበር?
4. ይህንን አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲያደርጉ ያስገደዳቸው ሁኔታ ምንድን ነበር?
5. የእነአቶ ሙስጠፋ ቤተሰብ ከአጉል ልማድ መላቀቅ እንዴት ቻሉ?
6. በእናንተ አካባቢ ወይም ቤተሰብ የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ምን ምን ተግባራት ይፈጸማሉ?

